# *ምንድነዉ ነገሩ ?*

**ለHR 2003**

*ከንጉሤ ጋማ*

ማን አለብኝ ንቀት፣ ዕብሪትና ትምክህት
መግቢያ መደበቂያ፣ መሸሸጊያ ያጡበት፣
አምባገነን ኃይሎች የባጡን የቆጡን የቀበጣጠሩት
ይይዙ፣ይጨብጡት መላዉ የጠፋቸዉ፣ ግራ የተጋቡት፣
ምንድነዉ ምስጢሩ፣ ምንድነዉ ነገሩ፣
እንዲህ ምጥ የሆንከዉ ገና ከጅምሩ?

ከኛ በላይ ላሳር ብለዉ እንዳላሉ
አስጥሉን፣ ገላግሉን፣አማልጹን እስኪሉ
ሽብር የፈጠርከዉ በፍርሃት ያስራድኸዉ
ወኔያቸዉን ሰልበህ ሱሪ ያስፈታኸዉ፣
ኸረ እንዲያዉ ምንድነዉ በስጋት አለቁ
ሕገ መንግስት ያህል፣ እንዳላረቀቁ፣ እንዳላፀደቁ::

ማንም መጣ ማንም ወደ መንግሥት ሥልጣን
ሠላም፣ ዲሞክራሲ፣ ብልፅግና እንዲሰፍን
ተጠያቂነቱ ግልፅነቱ እንዲኖር
ሕግ ብቻ ሳትሆን ሕግን ለማስከበር፣
ዋስትና መሆንህ ሃቁ ሳይጠፋቸዉ
ምንድነዉ ምስጢሩ እንዲህ ያመሳቸዉ?

የግምጃ ቤት ሠነድ አርገዉ የማይቆጥሩህ
እንደልማዳቸዉ ካንተ በላይ ሆነዉ፣ በንቀት የሚያዩህ
የማታፈናፍን፣ የማትሆን ሆንክና
ሣትታወጅ፣ ሣትፀድቅ፣ ሕግ ሳትሆን ገና፣
በረቂቅነትህ እንዲህ ከሚፈሩ፣ ከሚንጨረጨሩ
ምናለበት ቀድሞ ለሕግ ቢገዙ፣ በሕግ ቢኖሩ?